**CALGARY ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION**

**በካልጋሪ የኢትዮጵያ ኮምዩኒቲ ማሕበር**

# ሕብረት

**"Hibret", Monthly Newsletter**

ወርሃዊ ጋዜጣ

ቅጽ ፭ ቁጥር

ታህሳስ ፲፱፻፺፯

**Vol V No. 4 Dec 2004**

*In this Issue*

| | |
|---|---|
| የቦብ ማርሊን | 2 |
| በየመን እስር | 2 |
| .የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር | 3 |
| Somalia's angels | 3 |
| በየቀኑ 70 ሕፃናት ከኤች አ | 3 |
| የግብፅ ባለሃብቶች | 4 |
| ኢትዮጵያ በሞምባሳ | 4 |
| በኢየሩሳሌም | 4 |
| Advertisement | 5 |
| Advertisement | 6 |

## በአዲስ አበባና አካባቢዋ የሽቦ አልባ ቴሌፎን አገልግሎት በይፋ ተጀመረ

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን በ 10 ሚሊዮን ዶላር 42 ሺ መስመር ያለው ሽቦ አልባ የቴሌፎን አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ከትናንት በስቲያ ማታ በሸራተን ሆቴል ይፋ አደረገ፣ኮርፖሬሽኑ የሽቦ አልባ የቴሌፎን አገልግሎቱን ተግባራዊ ያደረገው ሁዋዌ ቴክ በኢትዮጵያ ከተባለው የቻይና ኩባንያ ጋር ባደረገው የአሥር ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ክፍያ ስምምነት መሰረት መሆኑን በዚሁ ወቅት ተገልጿል፣ከዚህ በተጨማሪ የሽቦ አልባ አገልግሎቱ ከስልክ በተጨማሪ የኢንተርኔትና የፋክስ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ የተዘረጋ መሆኑን አቶ አብዱራሂም አህመድ የኮርፖሬሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስኪያጅ ገልጸዋል፣ሽቦ አልባው ስልክ በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ በአርባ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኙ ከተሞች አገልግሎት መስጠት እንዲችል ሆኖ መዘርጋቱን አመልክተው፤ አገልግሎቱን በአስቸኳይ ለሚፈልጉ ባለሀብቶችና ኤክስፖርተሮች ለመስጠት ኮርፖሬሽኑ ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል፣የሽቦ አልባው ቴሌፎን አገልግሎት ሥራ ከተጀመረ አንድ ዓመት ያህል እንደሆነው አቶ አብዱራሂም ገልጸው፤ በአዲስ አበባ ውስጥ ለአንድ ሺ 400 ደንበኞች መስመሩ መሰጠቱን አብራርተዋል፣የሽቦ አልባው ስልክ ከነባሩ የሚለየው የኢንተርኔትና የፋክስ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ያለው መሆኑንና በመኪናም ሆነ ከመኪና ውጭ ከቦታ ቦታ እያንቀሳቀሱ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት መሆኑ ነው ብለዋል፣አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠይቀው የገንዘብ አቅም አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ብር ነው፣

ከአዲስ Ÿ መን ኅዳር 25 ቀን 1997

## Migrants die in icy sea crossing

Thirteen African would-be migrants have been found dead aboard a makeshift boat after a desperate attempt to reach the Canary Islands, Spanish officials said. They appear to have died from hypothermia after a three-day journey across icy seas in bad weather. At least three of 30 survivors are said to be in a bad condition in hospital.

Thousands of Africans try to make the treacherous journey every year, with many casualties. It is only a day since two people died in similar conditions. The dead were found on the boat by rescuers, sent to tow it after being spotted by police. Survivors clung to the bodies of their relatives, Spanish news reports said. A survivor told a photographer for the news agency AFP that the passengers had been sitting in frigid water since shortly after the boat left its undisclosed African port on Monday. The passengers were lightly dressed. A search mission for another boat which gave out a distress call would continue on Friday, said rescuers, according to AFP Three children are said to be on board. Shipping Africans to Europe is now booming business for smuggling mafias, now thought to be based largely in western Africa, correspondents say. At least 133 people are thought to have died crossing from West and North Africa this year alone.

## ኢትዮጵያዊት ወጣት በሊባኖስ ከፎቅ ተወረወረች

ገነት ሆቴል ግቢ ውስጥ በሚገኘው ሳብሬን ኤጀንሲ በኩል ወደ ሊባኖስ እንደሄደችና እዚያም እንደደረሰች «የዚህ አገር ኤጀንሲ እኔ ነኝ፤ የምትሠሪውም እኔ ዘንድ ነው» ብሎ የተቀበላት አረብ ለሌላ ሴት አሳልፎ እንደሰጣት ገልጣለች፣ ያቺም ሴት ተቀን ስለምትጨቀጭቃት ታማሚ መሆኗን ገልጻ ወደ ሀገሯ ለመመለስ ያቀረበችው ጥያቄ በቀጣሪዋ ተቀባይነት ማጣቱን የጠቀሰችው ሮዛ አንድ ሌሊት ምን እንዳስነኳት ሳታውቅ ከፎቅ ላይ ተወርውራ መውደቋን ከተኛችበት ሥፍራ ድረስ ሄዶ ላነጋገራት የነዋሪነቷ በልደታ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 04/36 በቤት ቁጥር 748 የሆነና ወጣት ሮዛ ሙዘሚል ሙዘይን የተባለች የ 19 ዓመት ወጣት በአሠሪዎቿ ከሦስተኛ ፎቅ ላይ ተወርውራ በአካሏ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባታል፣ወጣቷ ሐምሌ 29 ቀን 1997 ጋዜጣው ሪፖርተር ገልፃለች፣ አያይዛም «ከፎቅ ላይ እንደ ወደቅሁ ያነሱኝ የአምቡላስ ሠራተኞች አሠሪዬን በኔ ጠቋሚነት ሮዛ የታለች? ብለው ሲጠይቋት ተኝታለች» የሚል መልስ በመስጠቷ ለፖሊስ ሳያመለክቱ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል የወሰዱት መሆኑን አስታውቃለች፣«የወሰዱኝ ሆስፒታል ርካሽና በቂ ህክምና የማይገኝበት የነበረ ቢሆንም እኔ እሥራበት ከነበረው ፎቅ በላይ በነበረችው ኢትዮጵያዊት ጥቆማ ሌሎች ወገኖቼና የሀገራችን ቆንስል ጉዳዩን በመስማታቸው ከአንድ ቀን ቆይታ በኋላ 15 ቀን ወደተኛሁበት የተሻለ ሆስፒታል ተዛውሬያለሁ፣«እዚያም እያለሁ ፖሊሶቹ፣ ሀኪሞቹና ዓረቡ በመመሳጠርና ወንጀሉን ለመሸፋፈን ወደ ሀገሬ እንዳልሄድ አቆይተው ሊገድሉኝ በማሰብ ለቆንሲላው ኦፕራሲዮን እያደረግናት ነው የሚል መልስ ሰጡ እያሰቃዩን መቆየታቸውን ስላስጨነቀኝ ራሴን ለማዳን ስል ሴትየዋን ነፃ አውጥቼ በገዛ ፈቃዴ ከፎቅ ላይ መውደቄን ገልጬ ሀገሬ ለመመለስ ችያለሁ» ስትል እንባ እየተናነቃት ተናግራለች፣በሆስፒታል ቆይታዋ ከኢትዮጵያውያን ጋር እንዳትገናኝ በፖሊስ ስትጠበቅ መሰንበትዋን የጠቀሰው ሮዛ ክፍሏ ውስጥ የነበረው ስልክ ተቆርጦባት በአካልም በመንፈስም ክፉኛ

*(Continued on page 2)*

## ብእር ሲኮረኩር

### ቁጭት

ውጥኑ ስጋጃው የማዕረግ ስፌቱ
አክርማ ሰበዙ የአለላ ውበቱ
የሚሰፋው ጠፍቶ
የሚያስጌጠው አጥቶ
በአግባብ በስርዐቱ
ለመጋዣ ሲሳይ ዋለና በከንቱ
ማንፈሻ አገልግል መሶብም ጠፋና
አብነቱ ቁጭት ቤቱ ቀረ ኦና
ፍሬዘውድ ተስፋዬ (ቋጠሮ)
የጨዋ ልጅ ሁሉ ተዋርዶ
እንጨት ሰበራ ቆላ ወርዶ
ሲያነደው ያድራል ሌሊቱን
ቀን የሰበረውን፡፡

## Editorial

As this season is a holiday season, most of us don't go to our day-to-day work and rather it is time to exchange gifts, pass resolution for 2005 and connect with family members back home. The executive committee of Calgary Ethiopian Community Association would like to wish to all Ethiopians living in Calgary and surrounding areas a Marry Christmas (Melkam Gena) and a Happy New Year. CECA will celebrate this year Ethiopian Gena (Ethiopian Christmas which is on January 7) by organizing a holiday event to Ethiopian Children who are currently enrolled in the Amharic Language Class. The purpose of this event is to educate our culture to our children so that they can answer some of the identity questions that can arise any time in the future. CECA will welcome any new ideas that support our journey to become one of the strongest African ethnic communities in Calgary. We will appreciate if you can include your community in your New Year resolution as a place where you can start volunteering and contribute ideas.

*(Continued from page 1)*

*ኢትዮጵያዊት ወጣት ….*

ሲያሰቃዩአት መክረማቸውን አስረድታለች፡ባለፈው ቅዳሜ ሌሊት 6፡30 ሀገሯ ገብታ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሕክምና እየተደረገላት ያለችው ወጣት ሮዛ ከወገቧ በታች ያለው የመቀመጫዋና፣ የእግሮቿ አጥንቶች በመሰባበራቸውን በመሰንጠቃቸው መንቀሳቀስ እንደማትችል ገልፃልናለች፡

ከልሳነ [ § ዝብ ኅዳር 24 ቀን 1997 ]

**የቦብ ማርሊን 60ኛ ዓመት ልደት ለማክበር በመስቀል አደባባይ ግንባታ እየተካሄደ ነው**

የቦብ ማርሊን 60ኛ ዓመት የልደት በዓል ለማክበር በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የተለያየ የግንባታ ሥራ በመካሄድ ላይ መሆኑን አዘጋጅ ኮሚቴው አስታወቀ፡የልደት በዓሉ የቦብ ማርሊንና ሪታ ማርሊን ፋውንዴሽን «አፍሪካ ዩናይት » በሚል ከኢትዮጵያ መንግስት፣ ከአፍሪካ ህብረት፣ ከዓለም ባንክና ከተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት እንዲሁም ከተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ከመጪው የካቲት ጀምሮ ለአንድ ወር በሚቆዩ የተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል ፡በዓሉ በሲምፖዚየም፣ በሥዕል ኤግዚብሽን፣ በፊልም ፌስቲቫል፣ ለመላው ዓለም በቀጥታ በሚተላለፍ የሙዚቃ ኮንሰርት ይታሰባል፡በመላው ዓለም የሚገኙ የቦብ ማርሊ አድናቂዎች በአርቲስቱ መታሰቢያ ልዩ ዝግጅት ላይ ለመታደም አዲስ አበባ ይሰባሰባሉ ተብሎ ይጠበቃል፡በመስቀል አደባባይ ዝግጅቱን ለማቅረብ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ሥራዎች በማከናወን ላይ መሆናቸውን የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ገልጸዋል፡በመስቀል አደባባይ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በመጪው አዲስ ዓመት የካቲት 6 ቀን እንደሚቀርብ በሚጠበቀው የ 10 ሰዓታት የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ ከ 250 ሺ በላይ ሰዎች ይገኛሉ ተብሎ እንደሚገመት አዘጋጅ ኮሚቴው አስታውቋል፡

**CECA Memberships stand at 415**

## CECA'S CORNER

- Our regular **office hours** are:
  - **Mondays & Fridays: 6 to 9 pm**
  - **Saturdays: 9 am to 6 pm**
- We have new phone **(262 7260)** and fax **(262 9135)** numbers for our office. Please use this for any communication.
- Please send us your new babies & Wedding announcements as well as new graduates.
- Update your address with us. It is the most important information we need for effective communication with you.
- Please remember to send your membership dues.
- Send your suggestions for new project ideas to the CECA Executive Committee. **P.O.Box 22050, Bankers Hall, T2P 4J1**

**CECA wishes Orthodox Christians a happy Ghena (Jan 07) and Muslims a happy Id Al Adha in the coming days**

### Inaugural speech at opening of the first university in Ethiopia.

**"We are proud to see Ethiopian youth thirsting for learning. Although the fruits of education can be applied to evil as well as to good things, you Ethiopian students should avoid having a bad reputation and be eager and energetic in your studies, be loyal to your country and obedient to your teachers, eschew lies and follow truth, respect good and heirs of good work". Emperor Haile Selassie**

## በየመን እስር ቤቶች የነበሩ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ተመለሱ

በሕገ ወጥ ነዋሪነት ተይዘው በየመን እስር ቤቶች ታስረው የቆዩ ኢትዮጵያውያን ባሳለፍነው አርብ ወደ አገራቸው ተመልሰዋል፡ በቁጥር አንድ መቶ ያህል የሚሆኑት እነዚሁ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ጊዜያት እየተያዙ በእስር ቤቶች ለአንድ ዓመት ያህል ያለምንም ፍትሕ እንደቆዩ የገለጹ ሲሆን ንብረታቸውን ሳይዙ ያለምንም ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ በመደረጋቸው ችግር ላይ መውደቃቸውንም አመልክተዋል፡በየመን አየር መንገድ ወደ አዲስ አበባ እንዲወጡ የተደረጉት እነዚሁ ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ ከትግራይና ከአፋር ክልል በመሆናቸው ወደ አገራቸው መመለሻ ገንዘብ በማጣታቸው መቸገራቸውንም ጠቁመዋል፡

ከጦቢ[ያ ታኅሣሥ 21 ቀን 1997]

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን ለሦስተኛ ጊዜ ሻምፒዮን ሆነ

ከታህሳስ 2/1997 ጀምሮ በአዲስ አበባ ሲካሄድ በሰነበተው የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ እግር ኳስ ሻምፒዮና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለሦስተኛ ጊዜ አሸናፊ በመሆን ዋንጫውን አገሩ ላይ አስቀርቷል፡የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የተዘጋጀውን ዋንጫ ለመውሰድ የበቃው ትናንት የቡሩንዲ ብሔራዊ ቡድንን 3 ለ 0 በሆነ ሰፊ ውጤት ማሸነፍ በመቻሉ ነው፡ቡድኑ ከኬንያ ብሔራዊ ቡድን ጋር ለፍፃሜ ሲጫወት የታየበትን ድክመት ለማስተካከል ያደረገው ጥረት መሳካት የትናንቱን ውጤት በሚገባ ያሳመረው ሆኗል፡ብሔራዊ ቡድኑ ሻምፒዮናውን በድል በማጠናቀቁ ዋንጫ፥ የወርቅ ሜዳሊያና 35 ሺ ዶላር ተሸልሟል፡ ሁለተኛ የወጣው የቡሩንዲ ቡድን የብር ሜዳሊያና 20 ሺ ዶላር፥ ሦስተኛ የወጣው የሱዳን ቡድን የነሐስ ሜዳሊያና 10 ሺ ዶላር፥አራተኛ የወጣው የኬንያ ብሔራዊ ቡድን 5 ሺ ዶላር አግኝተዋል፡በስቴዲየሙ የተገኘው 30 ሺ የሚሆነው ተመልካች ለቡድኑ ውጤት ማማር ሲሰጥ የቆየው ጠንካራ ድጋፍ ፍሬ በማፍራቱ የተሰማውን ደስታ በጭፈራ ገልጿል፡ ሻምፒዮናውን ለሦስት ዓመታት ስፖንሰር ያደረጉት ክቡር ዶክተር ሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ዋንጫውን በአገሩ በማስቀረቱ ለእያንዳንዱ ተጫዋች 50 ሺ ብር ለመስጠት ቃል ገብተዋል፡ዶክተር ሼህ አል-አሙዲ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለስታዲየም መስሪያ ቦታ የሚሰጥ ከሆነ መዋእለ ንዋያቸውን በማፍሰስ የዜግነት ድርሻቸውን ለመወጣት ቃል ገብተዋል፡ሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫ ለማዘጋጀት እንድትችል የስታዲየም ግንባታው በመላው አገሪቱ ሊስፋፋ እንደሚገባ አሳስበዋል፡ በዚህ በኩልም ከሳቸው በኩል የሚጠበቀውን ሁሉ ለማድረግ መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል፡ በ 15 ቀን የተዘጋጀ ቡድን ዋንጫ ማግኘቱ መላው የኢትዮጵያ ህዝብን የሚያኮራ እንደሆነም ገልጸዋል፡ የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አርከበ እቁባይ በከተማው ለስተዲየም ግንባታ የሚውል መሬት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዘጋጅቶ ለፌዴሬሽኑ እንደሚሰጥ ቃል መግባታቸው በእለቱ ተገልጿል፡የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የኖርማላይዜሽን ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት፥ የኢትዮጵያ ህዝብና የውድድሩ ስፖንሰር ሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ ያደረጉት የጋራ ርብርቦሽ ባጭር ጊዜ ውስጥ የተሳካ ውድድር ለማዘጋጀት እንዳስቻለ ገልጸዋል፡ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ውድድሩ በመዘጋጀቱ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ትልቅ ደስታ እንደተሰማው ጠቁመዋል፡ ሼህ

ሙሐመድ አል -አሙዲ ተዳክሞ የነበረውን የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ የእግር ኳስ ሻምፒ

## Congratulations

Baby Heyab of Ethiopia & Mewaed



May you grow to make us all proud

## Somalia's angels of mercy

**By Joseph Winter**

**BBC News, Mogadishu**

An armed security guard sits at the entrance to the Hayat Hospital in the centre of Somalia's capital, Mogadishu, to ensure that no-one takes their weapons inside, turning a place of healing into a place of killing. And the doctors and nurses who work inside the hospital are only too well acquainted with the results of Somalia's 13 years of lawlessness. "Gunshots are one of our most serious problems," says Dr Mohammed Mahmut Hassan. But there is a sign of hope. He says that as the attempts to set up a new government have made progress, the number of gunshot victims has fallen. "We used to have 10 gunshot victims a day. Now, we see just four or five a month," he says. While Dr Mohammed is keenly waiting for the days when Somalia again has a government, the Hayat Hospital is also a sign of how well Somalis have coped without a central authority. He and other Somali doctors working abroad got together and in 1998 set up the hospital to try and fill the gap. "We had to help our people, even though we ourselves were safely living abroad," he said.

### Aids threat

In order to meet its running costs, the hospital charges for every visit - nobody is paying any taxes which could be used to provide a free service - but Dr Mohammed says they try to keep charges as low as possible. Every Friday, 200 people who cannot afford the $3 fee are treated free of charge and long queues form overnightWhile Hayat, and Mogadishu's four other hospitals, are able to provide a basic medical service, the Aids pandemic highlights the need for a government to tackle the problem at the national level, for example by running public awareness campaigns. The most recent statistics show that about 1% of Somali adults are HIV positive - low by African standards - but Dr Mohammed believes the numbers are rising quickly"We come across about five new positive cases every week," he says. One reason is the high number of Somalis living in refugee camps in the region, some of whom are now able to go home as fighting subsides. But Somalia remains a very traditional society, where Islam is strong and Dr Mohammed says that the hospital does not stock condoms - a key part of the fight against Aids - because the people do not accept them. "We can offer counselling but we cannot distribute condoms," he says. One hospital working alone will be unable to change such a deeply-entrenched mindset.

### Water lifeline

In another sign of the entrepreneurial spirit and self-reliance shown by Somalis, those Mogadishu residents with some form of income are also able to go to school and university and get running water and electricity. These are services not enjoyed by all of those who live in African cities with functioning governments. Until 2000, Hawo Mohammed Khalid got her water delivered in a barrel carried on a donkey cart. Now, she just has to turn the tap. "I feel happy now because I have water 24 hours a day. Before I might need water in the middle of the night and I didn't have any," she says. Hawo, married to one of the few Somalis with a regular job, also enjoys regular electricity - and says there are rarely any power-cuts. Her water and electricity are supplied by Abdoulkadir Hassan Issa, who runs the Isaf Water and Electricity Supply company in Bulo Hubey's south Mogadishu suburb. "We are doing this to provide a public service until the government comes," he says. "Then they can provide water and electricity or they might give us a contract and then we could continue. That's what we'd really like."

### Wire thieves

Mr Abdoulkadir says they used to use an open well but some customers complained about their water quality, so they dug a bore hole and add chlorine to prevent infection. It may not taste like mineral water but Hawo is not complaining. Generators provide electricity along very precarious-looking wires and Isaf has even hooked up fluorescent lights as makeshift street lamps. Isaf provides running water to 800 families and electricity to another 180 across a large part of south Mogadishu, he says. The biggest problem Mr Abdoulkadir faces is that thieves take advantage of the absence of law and order to steal the wires and pipes he used to provide his services. "But at least the militia which controls this area doesn't ask us for protection money," he says.

### 'Wait and see'

Nobody says that such services mean that a government is not needed but one western diplomat closely involved with the peace process says they mean "we must think out of the box for Somalia".

When a new government is eventually installed in Mogadishu, it would make no sense for it to take over all these services which are already functioning. "It would be a tragedy to fall into the trap of having a massive state sector, which would inevitably fuel corruption as we have seen elsewhere in Africa," he says. "Maybe the health ministry could set policies and targets for hospitals, which would remain in private hands, for example." But while arguments continue about how to bring the Kenya-based government back to Somalia, such questions remain academic. In the meantime, Dr Mohammed is not making any predictions about whether the fall in shootings will continue, or whether the latest attempt to set up a Somali government will fail, like the 13 which have gone before. "We're just waiting to see, like everyone else," he says.

## በየቀኑ 70 ሕፃናት ከኤች አይ ቪ ጋር ይወለዳሉ

ኢትዮጵያ ውስጥ በየቀኑ ቢያንስ 70 ሕፃናት ከኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ጋር እንደሚወለዱ የተባበሩት መንግሥታት ያወጣው ሪፖርት አመለከተ፡

ሪፖርቱ ጨምሮ እንደገለፀው ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በአለማችን ላይ በቫይረሱ የተያዙ ሕፃናት በከፍተኛ ደረጃ የሚገኙባት እንደ ሆነችና ይኸው ቁጥርም በየቀኑ እየጨመረ መሄዱን ነው፡ኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ ኤድስን ስርጭት ተገቢ በሆነ መንገድ መከላከል ካልቻሉ ሀገሮች ተርታ የምትመደብ ሲሆን ሌላው ቀርቶ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚያደርግ መድሃኒት እያለ ሕፃናቱን ከዚሁ ቫይረስ መታደግ አልተቻለም፡ አፍሪካ ውስጥ የቫይረሱ ስርጭት ከፍተኛ ከሆነባቸውና የኤድስ ስርጭት ከኢትዮጵያ የበለጠ ከሆነባቸው ሀገራት ጋር ሲወዳደር ቫይረሱ ከእናቶቻቸው የሚተላለፍባቸው ሕፃናት ቁጥር በኢትዮጵያ ውስጥ እየጨመረ የመጣ አሳሳቢ ችግር እንደሆነ ሪፖርቱ ጨምሮ ገልጿል፡እንደሚታወቀው በአሁኑ ሰዓት 4.6 ሚሊዮን ሕፃናት ከኤድስ ጋር በተያያዘ ወላጅ አልባ የሆኑ ሲሆን፥ እ.ኤ.አ በ 2004 ብቻ 500 ሺ ህፃናት ከበሽታው ጋር በተያያዘ ወላጅ አልባ መሆናቸውን ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡

ከŸ ሞኒተር ታኅሣሥ 15 ቀን 1997

## የግብፅ ባለሃብቶች እስራኤል ኢትዮጵያ ውስጥ በና ይል ወንዝ ልማት እንዳትሳተፍ ጠየቁ

በቅርቡ በግብፅና በእስራኤል መካከል አዲስ የዲፕሎማሲ ስምምነት ተደርሷል፡ በዚህ አዲስ ስምምነት መሰረት ግብጽ ከእስራኤል ጋር አቋርጣው የነበረውን የዲፕሎማሲ ግንኙነት ለመቀጠል የወሰነች ስትሆን በተጨማሪም የጋራ የንግድ ግንኙነት በተጠናከረ መንገድ ለመቀጠል ተስማምተዋል ፡ይህ ስምምነት ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ግን የግብፅ ባለሥልጣናት ከንግዱ ሕብረተሰብ ጋር ሰፊ ውይይት አካሄደው ነበር፡ በተለይ እ.ኤ.አ በታህሳስ 12 ቀን 2004 ዓ.ም የግብፁን የውሃና የመስኖ ሚኒስቴር አቡ ዛይድ የአገሪቱን የንግድ ሕብረተሰብ ተወካዮች አነጋግረው ነበር፡ በዚህ ውይይት ነጋዴዎች ከእስራኤል ጋር የሚደረገውን የንግድና የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከመጀመሩ በፊት እስራኤል ኢትዮጵያ ውስጥ የውሃ ልማት ሰፋ ላይ የምታደርገውን እንቅስቃሴ እንዲገለፅላቸው ጥያቄ አቅርበዋል፡ ሚኒስትሩ ለዚህ መልስ ሲሰጡ እስራኤል የአባይ ውሃ ድርሻችንን በሚቀንስ ትግበራ ላይ እንዳልተሰማራችና እንዲያውም አባይ ላይ ምንም ዓይነት ፕሮጀክት እንደሌላት አስረድተዋል፡ ሚኒስትሩ በተጨማሪም እስራኤል ኢትዮጵያ ውስጥ በውሃ ልማት ላይ የተሰማራችው የውሃ ጨዋማነትን በማስወገድ ላይ ትኩረት በመስጠት ነው ብለዋል፡

ከ፮ ዝባ ፮ ታኅሣሥ 09 ቀን 1997

## ኢትዮጵያ በሞምባሳ ወደብ ተጠቃሚ እንድትሆን መንገድ ሊገባ ነው

በመጪው የፈንጆች ዓመት ከኬንያ የወደብ ከተማ ከሆነችው ሞምባሳ ተነስቶ ኢትዮጵያ ድንበር የሚያገናኝ የመንገድ ግንባታ እንደሚጀመር የኬንያ የመንገድ ሚኒስትር መግለጻቸው አፍሮል ኒውስ ይፋ አደረገ፡አምስት ዓመታት ሊፈጅ እንደሚችል የተገመተው ይኼው ከሞምባሳ ተነስቶ በኢትዮጵያ ሞያሌ ድረስ ሊገባ የታቀደው ይህ የመንገድ ግንባታ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች መሀከል ንግድ ሥራዎች በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያድጉ ታስቦ ፕሮጀክቱ እንደተቀረፀ ይፋ ያደረጉት ሚኒስትሩ በተለይ ኢትዮጵያ የባሕር በር የሌላት ሀገር በመሆንዋ በጅቡቲና ሶማሊያ በረበራ ወደብ ለመጠቀም እንደተገደደችና በኤርትራ ወደብም እንድትጠቀም በሁለቱ ሀገሮች ባለው የድንበር ውዝግብ ምክንያት በመቋረጡ ለከፍተኛ ወጪ እየተዳረገች ትገኛለች፡ ነገር ግን በኬንያ ሞምባሳ ወደብ ተጠቃሚ እንዳትሆን ደረጃውን የጠበቀ የመኪና መንገድ በሁለት ድንበር መሀከል መገንባቱ ከጅቡቲና ሶማሊያ ወደቦች ባነሰ ክፍያ ተጠቃሚ እንድትሆን ያስችላታል ሲሉ ገልፀዋል፡

ከሰሜናዊ የኬንያ መንደር ኦስሎ ተነስቶ እስከኢትዮጵያ ድንበር ይዘልቃል ተብሎ የሚታሰበው ይኸው ደረጃውን የጠበቀና ከባድ ጭነት መቋቋም የሚችል መንገድ የአፍሪካ የልማት ፈንድ 51.6 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር እንዲሁም የኬንያ የመንግሥት በመደበው 3.9 ሚሊዮን ዶላር ወጭ እንደሚሸፍን የዘገበው አፍሮልኒውስ ግንባታው በ 2009 እ.ኤ.አ ተጠናቆ ሥራ ይጀመራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልጿል፡በርካታ የሥራ ዕድሎችን ይፈጠራልና እንዲሁም ኢንቨስተሮችን ቀልብ ለመሳብ ያስችላል፡ የአካባቢው ነዋሪ የኑሮ ገፅታ ይቀየራል ተብሎ በተገመተው በዚሁ የመንገድ ግንባታ እስካሁን የተገኘው 55 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ቢሆንም የፕሮጀክቱን ጥናት ይፋ ያደረጉት ድርጅቶችን ግን ከ 175 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል፡ ትራንስ አፍሪካ ሀይዌይ ከተሰኘው ፕሮጀክት አካል አንዱ እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን ካይሮን ኬፕታውን ድረስ የሚያገናኝ የመንገድም መገንባት የፕሮጀክቱ ውጥን መሆኑ ይፋ አድርጓል፡በቅርቡ በኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቀረበው አምስት ነጥብ ያዘለ የሰላም ሐሳብ ላይ «ሰጥቶ መቀበል» አጥብቀው በመግለጽ በርካታ የኅብረተሰብ ክአካል «በባድመን ሰጠን አሰብ እንቀበል ይሆናል» የሚል ሐሳብ በሰፊው በሚያናፍስበት በአሁኑ ወቅት ኬንያ ኢትዮጵያ ካለባት የወደብ ችግር ሳቢያ በሞምባሳ በኩል እንድትጠቀም መወሰኑና እንቅስቃሴ መጀመሩ «ሰጥቶ መቀበል» አሰብን የማያካትት መሆኑን ፍንጭ የሰጠ ጉዳይ ነው ሲሉ አንዳንድ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች የሰጡት አስተያየት ያመለክታል፡

ከጦማር ታኅሣሥ 06 ቀን 1997

## የአሌቲክስ መንደሩ በአይነቱ የመጀመሪያው ይሆናል

ወደፊት ለመገንባት በታቀደው የአትሌቲክስ መንደር የሚሰራው ጂምናዚየም ወደ 6000 ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን የጂምናዚየሙ ጣሪያ አሰራር በኬብል የሚወጠርና ምሰሶ አልባ በመሆኑ ግንባታው በኢትዮጵያ በአይነቱ የመጀመሪያ እንደሚያደርገው ተገለጸ፡የጠቅላላ ግንባታውን ዲዛይን ለመንደፍና ግንባታውን ለመቆጣጠር ከተወዳደሩ ሰስት የግንባታ ዲዛይንና አማካሪ ድርጅቶች መካከል አንዱ የነበረው ኤም.ኤች.ኢንጂነሪንግ የተባለው ኩባንያ ማሸነፉ የታወቀ ሲሆን፡ ይኸው ኩባንያ ባወጣው ዲዛይን መሰረት የጂምናዚየሙ ግንባታ 2000 ተመላካቾችን ማስተናገድ የሚችልና ምሰሶ አልባ እንደሚሆን የንድፉ ሀሳብ አፍላቂ የነበረው ወጣት አርክቴክት ፍስሃ አምሳለወርቅ እና የድርጅቱ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ዶክተር መሰለ ኃይሌ ለ ዘሞኒተር ጋዜጣ ገልፀዋል፡የአትሌቲክስ መንደሩ 400 የማደሪያ ክፍሎች የያዙ ህንፃዎች፡ እስከ 20000 ተመልካቶችን የሚያስተናግድ ስታዲየም፡ 2000 ተመልካችን የሚያስተናግድ የተለያዩ የቤት ውስጥ ስፖርት ውድድሮች የሚካሄዱበት ጂምናዚየም፡ እንዲሁም ለአስተዳደር አገልግሎት የሚውሉ ቢሮዎች፡ ሜንስ ቤቶችና ክሊኒኮች ያቀፈ ነው፡ይኸው የአትሌቲክስ መንደር ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ በሚገኘው በሰንዳፋ አካባቢ የሚቆረቆር ሲሆን ግንባታው እስከ 130 ሚሊዮን ብር ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፡

ከ፻ ሞኒተር ታኅሣሥ 01 ቀን 1997

## በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም እየታመሰ ነው

በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል የሆኑት አቡነ ቀውስጦስ በአቡነ ጳውሎስ ትዕዛዝ እንዲነሱ ትዕዛዝ በመተላለፉ በዚያ ያሉ የገዳሙ መነኮሳትና ሠራተኞች ተቃውሞ እንስተው መታመስ እየተፈጠረ መሆኑን ለቤተክህነት ቅርበት ያላቸው ምንጮች የተገኘ መረጃ ገልጿል፡ አቡነ ቀውስጦስ ከኢየሩሳሌም እንዳይነሱ በጥቅምት ወርተሰብስቦ የነበረው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ወስኖ እንደነበር

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ እግር ኳስ......

ዮና ስፖንሰር በማድረግ ለዳግም ውልደት እንዳበቁት በመግለጽ አመስግነዋል፡ አባል አገሮች ኢትዮጵያ ውድድሩን እንድታዘጋጅ በመተባበራቸውም አመስግነዋል፡ የሱዳን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ኢትዮጵያዊው ባለሀብት ሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ የዞኑ ውድድር ጠንካራ መሰረት እንዲይዝ በማድረጋቸው የተሰማቸውን ደስታ በመግለፅ ልዩ የመታሰቢያ ስጦታ አበርክቶላቸዋል፡በእለቱ ፕሮግራም ላይ በክብር እንግድነት በመገኘት ለአሸናፊው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የተዘጋጀውን ዋንጫ የሰጡት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ናቸው፡ በሥነ ሥርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ጊዜያዊ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አርከበ እቁባይ፡ የወጣቶች ስፖርትና ባህል ሚኒስትር አቶ ተሾመ ቶጋ፡ የአቅም ግንባታ ሚኒስትሩ አቶ ተፈራ ዋልዋ፡ የሴካፋ ፕሬዚዳንትና ሌሎችም የእግር ኳስ ባለሥልጣኖች ተገኝተዋል፡ሻምፒዮናውን በይፋ ሲዘጋ የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ አል-አሙዲ ሲኒየር ቻሌንጅ ካፕ እርግ ውድድሩን በቀጣይነት በ 2005 ለምታዘጋጀው አገር ሩዋንዳ ተሰጥቷል፡ የቀስተ ደመና ስፖንጅ ፋብሪካ ባለቤት አቶ አቤሴሎም ይሁደጉ በውድድሩ መሳካትና በተገኘው ድል የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ ለዶክተር አሸብር ወ/ጊዮርጊስና ለሼህ ሙሐመድ አል-አሙዲ ስጦታ አበርክተዋል፡

## በኢየሩሳሌም .....

እነዚሁ ምንጮች ጠቅሰው አባ ጳውሎስ ትዕዛዝ ያስተላለፉት የሲኖዶሱን ውሳኔ በመጋፋት እንደሆነም አብራርተዋል፡ይህ በአባ ጳውሎስ፡ በአባ ገሪማና «የፓትርያርኩ አማካሪ» ተብለው በተቀመጡት በአቶ ተድላ ተሾመ ተቀነባብሮ የተላለፈው ትዕዛዝ ሕገ ወጥ መሆኑን ምንጮቹ ጠቅሰው ለዚህ ሕገወጥ ድርጊት የመጀመሪያ ተጠያቂዎቹ ሦስቱ አካላት መሆናቸውን አስረድተዋል፡ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ከቦታው እንዲነሱ የተፈለገው ደብዳቤ እንደደረሳቸውም «የሾመኝ ቅዱስ ሲኖዶሱ እንጂ እርስዎ ባለመሆንዎ ሊያነሱኝ አይችሉም» በማለት ለአባ ጳውሎስ መልስ ከመፃፋቸውም በላይ በግልባጩም የኢትዮጵያ መንግሥት፡ በየመስተዳድሩ ያሉ ሊቃነ ጳጳሳት እያንዳንዳቸው እንዲያውቁት ያደረጉ መሆናቸውንም ከምንጮቹ መረዳት ተችሏል፡ለዚህ ሁሉ ሕገወጥ ድርጊት መነሻው ሊቀጳጳሱ በኢየሩሳሌም ያሉትን የዴር ሱልጣንንና ሌሎችንም ገዳማት ለማልማት በተለያዩ ሀገራት ከሌሎች የሰራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመዘዋወር ሀገር ወዳድ ከሆኑ ኢትዮጵያውያን ያሰባሰቡትን ገንዘብ አባ ጳውሎስ፡ አባ ገሪማና አቶ ተድላ ተሾመ ለመቆጣጠር በመፈለጋቸው የተፈጠረው ለመግባባት አንዱ ምክንያት እንደሆነ ምንጮች ይናገራሉ፡አባ ጳውሎስ በሀገር አሜሪካ በነበሩበት ወቅት የማርያምን ቤተክርስቲያን ለማሰራት ከምዕመናን ገንዘብ ተሰብስቦ በመባከኑ ሎሳንጀለስ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦባቸው እንደነበርና በዚያን ወቅት አብሮ ተከሶ የነበረው አቶ ተድላ ተሾመ እንደነበር ምንጮቹ ጠቁመው በነበራቸው ግንኙነት አሁን ወደ ፓትሪያርኩ ጽ/ቤት በቅጥር አስጠግተው በወር ከ 10 ሺህ ብር በላይ እየተከፈላቸው መሆኑን የጠቀሱት የቤተክህነት ምንጮች ግለሰቡ «ጳጳሳት የሚመሩበትን ህገ ቤተክርስቲያን አወጣለሁ» በማለትና ነባሩን የቤተክርስቲያኒቱን ሕግ ለማደስ እየሠሩ መሆኑን ገልፀዋል፡በኢየሩሳሌም «የይዞታ ይገባኛል» ጉዳይ ከግብፃዊያን ጋር ከፍተኛ ትግል በሚካሄድበት በአሁኑ ወቅት የቤተክርስቲያኒቱ መሪ ተብለው በተቀመጡትና በሌሎችም መታመሷ ለእምነቱ ተከታዮች ከፍተኛ ሀዘን መሆኑን ምንጮቹ አውስተው መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባላት፡ እንዲሁም በዚያ ከፍተኛ የልማት ተግባር የሚያከናውኑ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት በአንድነት ይህን ሕገወጥ አሠራርና ሌላውንም እንዲቃወሙ ምንጮች በማሳሰብ በተለይም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በአስቸኳይ ልዩ ስብሰባ አድርገው የፓትርያርኩን ሥልጣን እንዲገድቡ ተማጽነዋል፡

ከጦማር ኅዳር 22 ቀን 1997

## መጪው የህይዎትዎ ዘመን ብሩህ እንዲሆን  ይፈልጋሉ?

በየጊዜው የሚለዋወጠውን የባንኮች አሰራርና የፋይናንስ ገበያ እንቅስቃሴ በሚገባ ተረድተው ተገቢውን እቅድ በማውጣት ብሩህ የህይወት ጎዳና ለመምረጥ የግድ በፋይናንስ አያያዝና እቅድ በቂ እውቀትና ከመንግስትም የአማካሪነት ፍቃድ ያላቸውን አዋቂዎች ማነጋገር እጅግ ጠቃሚ ነው።

ስለሆነም ስለማንኛውም የገንዘብ አያያዝና እቅድ ጉዳይ ፤ ስለ እስቶክ ገበያ እንቨስትመንት ፤ ስለ ጡረታ የቁጠባ ፕሮግራም ፤ ስለ ልጆች የወደፊት የትምህረት ወጪ የቁጠባ ፕሮግራም ፤ ፤ ለቤት ግዠ ከባንክ በጥሩ ወለድ ብድር ስለማግኘት ወይም በጥሩ ወለድ ሞርጌጅ ስለማሳደስ እና ስለ ማንኛውም እንሹራንስ ከዚህ በታች በተጠቀሰው የስልክ ቁጥር በመደወል ከባለሙያ ምክርና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

**403 266 2061 የውስጥ መስመር 251**

**ዶ/ር ግርማ ሉሉ**

**የሳን ላይፍ ፋይናንሻል እና የክላሪካ ተወካይ**

**ለበለጠ ማብራሪያ www.Clarica.com/girma.lulu ፡ይመልከቱ**

### ብሩህ የህይወት ጎዳና ግልጥ በሆነ እቅድ ይጀመራል ።

## መልካም የገናና የተሳካ 2005 ዓመት እመኛለሁ!!

# Clarify
# your
# future.

Making the right choices in the confusing world of finances requires clarity. That's where I come in. As your Clarica advisor, I'll work together with you to develop a plan that's clearly right for you.

**There's a lot to be said for clarity.**



*Girma Lulu, PhD.*
*Bus (403) 266-2061 ext 251*
*Res (403) 208-9732*
*Fax (403) 262-6609*
*girma.lulu@clarica.com*
*5980 Centre Street SE, Calgary AB T2H 0C1*

CLARICA

*Investment and insurance solutions - since 1870*

*life, health & disability insurance, savings and retirement plans, employee benefits, mortgage & business insurance*

Associated with Clarica Financial Services Inc.

Copyright © 2004 CECA

# *!!Welcome to2005!!*

**New year, fresh beginning! Interest rates remain low and inventory of homes are stable. It is a very good time for both first-time home buyers and sellers who are upgrading!**

**<u>BUYERS:</u>**

Before you go anywhere else CALL ME and I will:

- Provide free consultation regarding every aspect of home buying
- Help you find the best mortgage financing, legal service, home inspection.
- Assess your situation and find you a home that meets your needs within your budget.
- Work with you patiently, diligently and with complete professionalism and utmost confidentiality for as long as it takes! Your satisfaction is my priority.
- Do an independent Market value analysis of the home you choose, if necessary, so that you know what the house is worth before you make an offer!
- In short, does everything I can to make your home-buying experience as smooth and pleasant as it can possibly be!.....and the best thing about it is IT WON'T COST YOU <u>ANYTHING!!</u>

**<u>Sellers:</u>**

When you sell your home through me you can do so with confidence! I will:

- Have a pre-listing consultation with you to find out exactly what your plan is in order to market your house appropriately
- Advise you on what to do to make your home sell faster
- Provide a complete market value analysis and give you my honest professional assessment of what your house is worth.
- Use the latest technology available to market your home.
- Be available to you 24 hrs a day 7 days a week until the house is sold!
- Give you the most competitive rate for my services
- Make sure confidentiality is guaranteed!

“Service a TAD above” is not just a slogan but my commitment to you!

So call today @ 815-4394 and ask for Tad. I want to do business with you, honestly.

MaxWell

TAD MULUGETA
Real Estate Agent
MaxWell Classic Realty
An independent member broker

#525, 500 Country Hills Blvd. NE
Calgary, Alberta T3K 4Y7
Bus: (403) 226-9318
Fax: (403) 226-8566
Cell: (403) 815-4394
Email: tmgeta@shaw.ca





Copyright © 2004 CECA